# <u>ጥሪ !</u>

**<u>"ግለሰብ የሀገርና የህዝብ ቅንጣት ነው ፣ በግለሰብ ስቃይ ላይ ያለን አቋም በአገር ና በህዝብ ላይ ያለ አመለካከት ነፀብራቅ ነው "</u>**

ዘለሌ ፀጋስላሴ ወያኔ ኢትዮጲያን ከተቆጣጠረበት ጊዜ አንስቶ  የዕድሜ ፍላጎቶች ሳያሳስቱት ለማንኛውም የግል ጥቅም ሳይደለል፣ከምንም ከማንም በላይ የአገሩን ጉዳይ በሚያስቀድም ፅናቱ የሚታወቅ እስከዛሬም በዚሁ በማያዋለዳ አቋሙ ፅንቶ የሚገኝ ጀግና ነው ።

ስለዘለሌ ለማስታወስ ካልሆነ በአገራዊ ፖለቲካ በ20 አመት ውስጥ ያለፋባቸው መንገዶች እና ያሳለፋቸው ውጣውረዶች በሙሉ ለመግለፅ ዳጎስ ያለ ጥራዝ ያለው መፅሐፍ መፃፍ ያስፈልጋል ። ማለት ካለብን  "ዘለሌ ለዓላማው ታማኝ፣ ቅንና የሃገር የህዝብ ፍቅር ያለው ኢትዮጲያዊ ጀግና ነው  " ብንል ምናልባት ይህ አባባል ማንነቱን ሊገልፅልን ይችላል።

ዘለሌ በ1987 በወያኔ በተዘጋጀው የህገ-መንግስት ጉባዔ ከ500 በላይ የወያኔ ጭፍሮች መሃከል በድፍረት  " አይሰራም ህገ-መንግስቱ የደደቢቱ ማለቱ " ከዚያም በላይ በድንበር ፣ በሰንደቅ ዓላማ ፣ በአንቀፅ 39 ........ ወዘተ ያቀረባቸው እምባ ቀረሽ ሙጉቶች ቡዙዎቻችን እስከዛሬ እናስታውሰዋለን ። በጉባዔው ፍፃሜም በሸፍጥ ሰነድ ላይ አልፈርምም በማለት በህገ-መንግስቱ መፅደቂያ ስምምነት ሰነድ ላይ ፊርማውን አላዋለም ። በዚህ ብዙ መከራ እንደደረሰበት በወቅቱ ትኩስ ዜና ሆኖ ተዘግቧል።

በ1987 በተደረገው የአንደኛው ዙር የህዝብ ተወካዮች ምርጫ በዕጩነት ተመዝግቦ በርካታ የድጋፍ ፊርማ ካሰባሰበ በኋላ " የሞተ ሰው አስፈርመሃል" በሚል አሳፋሪ ክስ ከምርጫው እንዲሰረዝ ተወስኖበታል ። ዘለሌ ጉባዔው ላይ በነበረው ጠንካራ አቋም ቂም ተይዞበት ይህ እንደሆነ ቢያውቅም የሞተሰው ማስፈረም ከቻልኩ በዓለም የድንቅ ስራዎች መዝገብ ላይ መመዝገብ ይገባኛል በማለት ያስተላለፈው መልእክት በተለያዩ ጋዜጣዎች / ቃለ መጠየቅ ጭምር / ተዘግበው እንደነበር ይታወሳል። በ1992 ኢ.ዴ.ፓን ከመሰረቱ ወጣቶች  እና በአመራሩ ከተባረሩት አስራ አንድ ወጣቶች አንዱ ነው ። በወቅቱም ማንም ያላየውን ችግር በማሳየት እነ ዘለሌ ያደረጉት ትግል የሚረሳ አይደለም ።

ከዚህ በኋላ መ.ኢ.ዴ.ፓን በመመስረትና በፕሬዚዳንትነት ፓርቲውን ሲመራ ቆይቷል። ከ1997 ምርጫ ተከትሎ በርካታ መከራዎችን በማሳለፍ በተለይም በግል ህይወቱ የንግድ ፍቃዶቹ ተሰርዘውበት የንግድ ድርጅቶቹ ተዘግተውበት / እስከ ዛሬም እንደተዘጉ / በአገራችን የፍትህና የነፃነት እጦት ህያው ምስክር ለመሆን በቅቷል ።

ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ወያኔ ለአመፅ እንቅስቃሴ አይመለሱም በሚል የጥርጣሬ ክትትል ሲያደርግባቸው ከነበሩት መካከል አንዱ እሱ መሆኑንን የተረዳው ዘለሌ የ2002 ምርጫ ለይስሙላ ለመስታፍ ፓርቲውን  አስመዝግቦ እንቅስቃሴ ለማድረግ ሞክሯል። ወያኔ በጥርጣሬው ገፍቶ  በመሄድ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ለጥያቄ በሚል ዘለሌ ያልተወሰደበት ጣቢያና የደህንነት ቢሮ አልነበረም ። በመጨረሻም በምርጫው ዋዜማ ቀን በደህንነቶች ታፍኖ ተደብድቦል በዕለቱም  በየክርክሩና በግሉ ስልክ ያደረጋቸው ንግግሮች ቀድመው በመቅረፀ ድምፅ የቀዱትን በማሰማት ከአገር መውጣት አትችልም የሚል ዉሳኔ ተነግሮታል ። ዘለሌ በአውሮፓ ህብረት ታዛቢዎች ጫና ከእስር ቢለቀቅም ህይወቱ አደጋ ውስጥ መሆኑ ግልፅ ሆኖለታል ።

ዘለሌ ግንቦት 2002 መጨረሻ ከአገሩ ተሰዶ በእልህ አስጨራሽ ጉዞ ኬንያ ቢደርስም ጥገኝነት አልጠየቀም ። ረጅም አላማ አንግቦ ተስፋ ሰንቆ ኡጋንዳ ገባ። ዘለሌ በአሁን ሰዓት ከ23 ንፁሃን ዜጎች ጋር በአሸባሪነት ተከሷል። ይህ ደግሞ ዘለሌን ብቸኛው በአፍሪካ የሚኖር የሽበርተኝነት ክስ  ተከሳሽ ያደርገዋል ። አርቆ ማየት የተሳናቸውን ያላሳሰበው የሚመስለው ይህ አደጋ ቡዙዎቻችንን ያስጨንቀናል ፤ አስደንጋጭ ልምድ አለንና ።

በቅርቡ ወያኔ አንዱአለም አያሌው የተባለ እንደ ዘለሌ ተመሳሳይ ክስ የቀረበበትን ከሱዳን አፍኖ ወስዶል። **የዘለሌ እጣ ምን ይሆን ?ዘለሌ ላይ የተጋረጠው አደጋ ለሌሎቻችንስ የሞራል ጥያቄ አያስነሳም ?**

በአሁን ሰአት ዘለሌ የሚኖርበት አካባቢና በተለይም የሚኖርበት ጎስቋላ ጎጆ ለአገራዊ ጉዳይ የቆመ ዜጋን የማይመጥን ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ለአደጋ የተጋለጠ መሆኑ ያሳስባል ።

ዘለሌ ደጋፊ አጥቶ መሰረታዊ ፍላጎቱን ማሟላት ተስኖት  ከልጁ ጋር በከፍተኛ እንግልት ላይ ይገኛል። **በዚህ ዙሪያ ዘለሌ እንዲገለፁ ያልፈለጋቸው ቅሬታዎቹ በእርግጥ ለጊዜው ተከድነው ቢያድሩ ይሻላል ።**

ችግሩ በጋራ ጉዳይ ምክንያት የደረሰበት በመሆኑ እጅግ ያሳዝናል ! ያሳዝናል !! ከዛም በላይ  መከራውን ላለመካፈል ማፈግፈግ እጅግ ያስፈራል ! ያሳፍራል !!

በጠላት እረጅም እጅ ምክንያት UNHCR UGANDA የዘለሌ ዓይነት ታዋቂ ሰዎች ጉዳይ የማድመጥ ፍላጎት የለውም ።

ስለዚህ ይህ ኢትዮጲያዊ ጀግና ከነልጁ አስተማማኝ መጠለያ አግኝቶ መሰረታዊ ፍላጎቱ የሚሞላበት ሁኔታ መፍጠር እንዲሁም በስደተኞች ዙሪያ ላይ የሚሰሩ   UNHCR ፣ HIAS .... አስቸኳይ ዘላቂ መፍትሄ እንዲሰጡት መጮኸና መታገል የማንም ስራ ሳይሆን የእውነተኛ ኢትዮጲያዊያን አገራዊ ግዳጅ ሊሆን ይገባል ።

ስለሆነም በየትኛውም የዓለም ክፍል የምታገኙ ሃገር ወዳዶችና የኢትዮጲያ ችግር የሚያንገበግባችሁ ዜጎች ይህንን ጀግና በፋይናንስ ፣ በማቴሪያል ፣ በሃሳብ ...... ፈጣንና እጅግ አስቸኳይ ድጋፍ በማድረግ ከተጋረጠበት ጥቃት ለመታደግ በወቅታዊ ችግሮቹ ላይ ለመድረስ ርብርቦሽ እናደርግ ዘንድ አገራዊና ወገናዊ ጥሪ እናስተላልፋለን ።

" ዘለሌን በመደገፍ በትግል ውስጥ ላሉትና ወደ ትግሉ ለሚቀላቀለው አዲስ ትውልድ ወገናዊ ደጀንነታችንን እናስመስክር "

ዘለሌን ማግኘት ለምትፈልጉ ፤

ስልክ ቁጥር  +256717644399 , +256792875284

ለድጋፋችሁ የባንክ ሂሳብ ቁጥር

Zelelie tsegaselassie

Equity bank , kabalagala branch

Account number : 1035100635942

Uganda , Kampala

<u>በራስ ተነሳሽነት አስተባባሪዎች</u>

1 ተስፋሁን ክብረቴ  (አቶ )

2 አበራ ጉርሙ ( ኮ/ል)

3 አለምነሽ በረዳ (ወ/ሮ )

**" ስለ በጎ ምላሻችሁ ወገናዊ ኩራታችን ከፍ ያለ ነው "**